# ደመራ


ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

መስከረም 11 ቀን 2007 ዓ.ም.

nigatuasteraye@gmail.com


## እንኳን ለዘንድሮው የደመራ በዓል አደረሳችሁ! አደረሰን!

ሰላሙ የደፈረሰበት ህዝብ የመንፈስ ጤንነት አይሰማውም። ሰላምና ጤና የሚነጣጠሉ አይደሉምና፤ የመንፈስ ጤንነት የደፈረሰበት ህዝብ ጤናማ ነው ማለት አይቻልም። "ሰላም ሳይኖር ሰላም የሚሉ ወዮላቸው!" ከሚለው ከነብያት ቃል ጋራ ተጋጨ። ይህም ብቻ አይደለም። ሰላም የሌለን ቄሶች ሰላም እንደሌለን እያወቅን፤ የተቀጠርንለት እለታዊ ገቢያችን እንዳይቀርብን " ሰላም ለኩልክሙ" እንላለን። በጥቅሉ ልማድ አድራሾች ሆን። የተዋህዶ እምነት ተከታዮች ነን የምንል ኢትዮጵያውያን ሰላም ምንጭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊወህደን ቀርቶ አልተቀበልነውም። ከዚህ ዓመት የደረስነው አሁን ያለንበት "በደብረ ሰላም ኢይኩን ህከክ" ማለትም፦ በደብራችን ህውከት ብጥብጥ አይኑር" እያልን ጉሮሯችን እስኪሰነጠቅ የምንጮኸው ላምድ ለማድረስ ብቻ ነው። ስለዚህ "እንኳን አደረሳችሁ" እንጅ "እንኳን በሰላምና በጤና አደረሳችሁ" ማለት መዋሸት ነው።

አምና መስከረም ፳፻፬ ዓ.ም. (September) 24, 2014 07:07 ደመራ በሚል ርእስ "በሃይማኖታችን፥ በታሪካችንና በባሕላችን አንጻር" አቅርቤው በየድረ ገጾች ተነቧል። የደመራው በዓል የዘመን ርቀት ያማስረሰው በያመቱ የሚታወስ ቢሆንም፤ በእሌኒ ታሪክ ብቻ ተሸፍኖ ሰረዛዊ ታሪክነቱ (ኢትዮጵያዊነቱ) ተሰውሯል። በዚህ ዓመት የገጠመንን እንቃኝበት ዘንድ፤ አምና የተሰወረው ታሪካችን ለማንጸባረቅ "በታሪካችንና በባሕላችን አንጻር" በሚል ርእስ ስለደመራ በዓል አቅርቤ ነበር። ሙሉውን ለማንበበ ከፈለጉ ወደ ከንሳስ መድኃኔ ዓለም ድረ ገጽ በመሻገር ያገኙታል። ዘንድሮ ደግሞ የገጠመንን ለማንጸባረቅ አምና ካቀረብኩት ጨልፌ እንዳቀረብላችሁ ያለንበት ሁኔታ አስገደደኝ ።



## ደመራ በታሪካችንና በባህላችን አንጻር

የደመራውን በዓል መሠረታዊ መነሻ የጀመረችው በአራተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ እሌኒ የምትባለው የቆስጠንጢኖስ እናት ናት። የጀመረችበት ምክንያትም የክርስቶስ ተቃራኒዎች፥ የክርስትና ንክኪ ያለውን ፍንጭ ሁሉ ለማጥፋት ባደረጉት ጥረት፥ ከክርስትና ፍንጮች አንዱ የክርስቶስ መስቀል በመሆኑ በጉርጓድ ቀበረውት ነበረና ፈልጋ ለማግኘት ነበር።

መስቀሉን ለማግኘት የተጠቀመችበት ስልት፥ እሳት አንድዳ ጢሱ እንዲመራት በመጸለይ ነበር። የሚቃጠል ነገር ሰብስባና ደምራ በማንደድ ጢሱን ተከትላ በመሄድ መስቀሉን አገኘችው። እንዴት እንዳገኘችው በያመቱ ስንናገረው የኖርነው ነውና፥ ሙሉ ታሪኩን እዚህ ላይ ገትቼ፥ ጥንታውያን አባቶቻችን ከራሳችን ታሪክ ጋራ አዋህደው እንዴትና ለምን እንደተጠቀሙበት ካባቶች የሰማሁትን ለማስታወስና የዘንድሮውን አጋጣሚ ለመግለጽ ነው።

## ካባቶች የሰማሁት

የመስቀል በዓል ከታሪካችን ጋራ እንዴት እንደተያያዘ አባቶች እንዲህ ይገልጹታል። ንግሥት እሌኒ የተቀበረውን መስቀል ለማግኘ በጀመረችበት ቦታና ህዝብ ፥ እኛ በምናደርገው ሥርዓት ዓይነት ሊከበር ቀርቶ የሚያስታውሰውም የለም። ለምን እኛ ብቻ ከክርስቲያኑ ዓለም በተለየ መልክ እናከብረዋለን? የሚል ጥያቄ ማስከተሉ አይቀርም። የደመራውን ታሪክ የማስተማርና በደመራው ዙሪያ ለሚነሱት ጥያቄዎች የመመለስ እዳ፥ ሸክምና ግዴታ ያለባቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ታዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባዔ የዋሉ ብቻ ናቸው።

ለነገሩማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያኖች በተለየ መንገድ የምናከብረው የደመራን በዓል ብቻ አይደለም። የጥምቀቱን በዓልም ሆነ ሌሎችን በዓላት ከዓለም ክርስቲያኖች ለየት ባለ መንገድ እናከከብራቸዋለን። ከዓለም በተለየ መንገድ በዓላትን የምናከብርበት ምክንያት፤ ከመነሻቸው ሌላ ሰረዝነት ያላቸው የተደራረቡ ታሪካውያን ክስተቶች ናቸው። በስነ ፍጥረት በቅዱሳት መጻህፍትና በታሪክ ምርምር የበለጸጉ የቅኔ መምህራን እንደነገሩን፤ በዓላት እንደ ዓባይ፤ ሙጋና ሱሀ የመሳሰሉ ወንዞች፤ ካንድ ቦታ መንጭተው በየደረሱበት የሚቀላቀላቸውን ትናንሽ ወንዞችንና ወቅታውያን ጎርፎችን እየተሸከሙ የሚጓዙ ናቸው። ሰውም እንስሳትና እጽዋትም ቢሆኑ በዚህ መንገድ ቅብብሎሽ የመጡ ናቸው። ይህም የተፈጥሮ ሂደት የተደራረበ ምሥጢር አዘል ቅኔ ሠረዝ ይባላል።

የደመራውን በዓል የጀመረችው እሌኒ፤ ደመራ ብላ አልሰየመችውም። ወደኛ ተሻግሮ ደመራ ብለን በምናከብረው ሁኔታና መንፈስ ሰፍቶ ከመከበሩ በፊት፥ እስከ አጼ ገላውዴዎስ ዘመን በኢትዮጵያ ይከበር የነበረው የመስቀል በዓል እየተባለ ነበር። በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን አዲስ ታሪካዊ ክስተት ገጠመው። ሊቃውንት አበው የገጠመውን አዲስ ክስተት ከመስቀሉ በዓል ጋራ በመደመር የበዓሉን ስም ደመራ ብለው እስከኛ ዘመን እየተከበረ ቆይቷል።

ይህ በዓል ንግሥት እሌኒ በጀመረችበት ቦታና ህዝብ ፥ እኛ በምናደርገው ሥርዓት ዓይነት ሰረዝነት ባለው መልኩ ሊከበር ቀርቶ የሚያስታውሰውም የለም። ለምን በእኛ ሰረዛዊ ሆነ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ

እሌኒ በጀመረችበት ቦታና ህዝብ በመሰረታዊ ባህርዩ እንኳ እንዲቀጥል እድሉን በማጣቱ ነው። በተጀመረበት ቦታ የነበሩ ሰዎች ዘራቸው ጨርሶ ጠፍቷል ባይባልም፤ በተለያዩ ምክንያቶች ከቦታቸው ተፈናቅለዋል። ወይም በባእድ ተውጠዋል። ወይም እየፈለሱ በባእድ አገር ተበትነዋል።

የሰረዝ ቅኔ ሊቃውንት አባቶቻችን እንደነገሩን፤ ባንድ ወቅት የተጀመሩ ጥንትነት ያላቸው ነገሮች ሰርጎ በሚገባ ባእድ ካልተደናቀፉና ከልተቆራረጡ፤ ወርቅ ሆነው ለሚከሰቱ አዳዲስ ነገሮች፤ ስም እየሆኑ እስከ ህልፈተ ዓለም ይቀጥላሉ። <u>ይህ የሆነበት ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ ከቦታው ተፈናቅሎ ባለመበተኑና በውጭ ሰርገው በሚገቡ ባእዳን ትጥቁን ሳይፈታ እሱነቱን ሳይረሳ ተረጋግቶ በመኖሩ ነው።</u> ባንድ ወቅት የተዘጋጁ መጻሕፍት በውስጣቸው የያዙትን ምዕራፍ በሚገጥሟቸው ተመሳሳይ አዳዲስ ክስተቶች እየሰፉ በመደጋገም እንደሚታተሙ፥ በዚህ መልክ <u>በየአመቱ በመመላለስ የሚታወሱ ሁሉ በዓላት፥ በየደረሱበት የዘመን ርከን የሚገጥሟቸውን በመደመር ይዘታቸው እየሰፋ የሕብረተ ሰቡን ትዝታ፤</u> ድካምና ብርታት በየዘመኑ ያለፈበትን ሁሉ ውጣ ውረድ ዝክረ ነገር (<u>Social Memory)</u> የተሸከሙ ናቸው።

## <u>ከ ታሪክ ጋራ እንዴት ተወሀደ</u>

*ከሊቃውንት አበው መምሕሮቼ እንደሰማሁት፥ ግራኝ መሐመድ ኢትዮጵያን በወረራት ዘመን፥ የአገሪቱ መሪ አጼ ልብነ ድንግል በዚያ ዘመን ገናና ይባል የነበረውን የፖርቹጋሉን መንግሥት እርዳታ ጠየቁ። የፖርቹጋሉ መንግሥትም ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ፦*

- *፩ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በሮማ ካቶሊክ ፓፓ ሥር ለማድረግ፥*
- *፪ኛ ኢትዮጵያን በራሱ ቅኝ አገዛዝ ሥር ለማድረግ ከሮማው ፓፓ ጋራ ተንኮል ሲሸርብ ዘገየ።*

*የዘመኑ የጉዞ ሁኔታም ለመዘግየታቸው ተደማሪ ችግር ነበር ይላሉ። የፖርቱጋል ሰዎች አጼ ልብነ ድንግል ከጠየቁበት ወቅት እጅግ ዘግይተው፥ ጦርነቱ ካለቀ በኋላ ኢትዮጵያ ደረሱ። አጼ ልብነ ድንግል ሞተው፤ አጼ ገላውዴዎስ የመሪነቱን ቦታ ወስደው፤ በጦርነቱ የደቀቀው ሕዝብ በመቋቋም ላይ ሳለ፥ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ፖርትጋሎች ወደ አገራቸው በመመለስ ፈንታ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ በመኖር በሕዝቡ መካከል እየገቡ፥ አሁን ቻይናዎች በአገራችን ላይ እንደሚያደርጉት ማለት ነው፥ ኢትዮጵያውያን ሴቶችን እያገቡ በመዋለድ ኑሯቸውን በኢትዮጵያ ምድር ማስፋፋት ጀመሩ።*

*ከመከራው ሳያርፍ ገና በመቋቋም ላይ ሳለ እንደገና ፖርቹጋሎች ከፈጡሩበት መከራ ውስጥ ገባ። በፖርቹጋሎችና በኢትዮጵያውያን መካከል ጥላቻውና መናናቁ እጅግ በማየሉ በቅጽል ስምና በተረብ መዘላለፍ ተጀመረ። <u>ኢትዮጵያውያን የፖርቱጋሎች ባህርይ ለመግለጽ ትኋን የሚል ስም ሰጧቸው። ፖርቱጋሎች ደግሞ የኢትዮጵያውያን ባህርይ ለመግለጽ ቁንጫ የሚል ስም ሰጧቸው።</u>*

*በመናናቅ እርስ በርስ የተሰጣጧቸው የቅጽል መግለጫዎች ትርጉም አላቸው። ኢትዮጵያውያን የፖርቹጋሎችን ጠባይ በትኋን ጠባይ የገለጿቸው፥ <u>ትኋን የሰው ደም መምጠጥ የምትጀምረው ጨለማ ተንተርሳ፥ ከየስርቻው እየተሳበች በመውጣት ነው።</u> ደሙን የመጠጠችው ሰው ካገኛት ከመደፍጠጥ ሮጣ አታመልጥም። <u>የመጠጠችውን ደም ተሸክማ ስትንገዳገድ ትደፈጠጣላች። ከተደፈጠጠች በኋላ</u>*

የሚቀረው ክርፋት በቀላሉ የማይለቅ  እጅግ አስከፊ ነው።  ኢትዮጵያውያን ፖርቹጋሎችን እንዲህ ናችሁ ለማለት  ትኋኖች ብለዋቸዋል።

ቁንጫ  ቀንም ሌትም አትመርጥም። ይዞ ለመግደልም የማትጨበጥ ፈጣን ናት። የሚሸት ነገር የላትም። ኢትዮጵያውያኖችንም አይያዙም፥ አይጨበጡም፥ ጠላታቸውን ለማጥቃት ቀንና ሌሊት አይሉም ለማለት፤  ፖርቹጋሎቹ ኢትዮጵያውያንን ቁንጫዎች ብለዋቸዋል። በዚህ መልክ በኢትዮጵያውያንና በፖርቱጋሎች መካከል መሰዳደቡና  መተራረቡ አድጎ ጸቡና ጥላቻው እየከረረ ሄደ።  በቀረው ክፍል ሰፍረው ይኖሩ ከነበሩት ይልቅ በአድዋ አካባቢ የነበሩት ፖርቹጋሎች እጅግ ደርጅተው  የጠነከረ መሰረት ነበራቸው። በኢትዮጵያውያን መካከል የነበረው ህዝባዊ ግንኙነት እንዳሁኑ ፈጣን ስላልነበረ፤ ባንድ አካባቢ የሚደርሰው መከራም ሆነ ደስታ  በሌላ አካባቢ የሚደርሰው ዘግይቶ ነበር። ፖርቱጋሎች ይህን በመጠቀም፤  በሌላ አካባቢ ያለው ሁሉ ኢትዮጵያዊ የፖርቱጋሉን መንግስት አገዛዝ በመቀበል  በሰላምና በደስታ ይናርል። እናንተ ብቻ ናችሁ ከመላው ኢትዮጵያ ህብረተ ሰብ ተቆርጣችሁ የቀራችሁ”  እያሉ በመስበክ በየዋህነት ተሎ የተቀበላቸውን ህዝብ የነቃ አዕምሮ ካለው ወገኑ ከፈሉት። እርስ በርሱ በማጣላት የማገዳደል ደባ በአድዋ ሕዝብ ላይ የፈጸሙት እጅግ የከፋ ነበር ይባላል።

ይህን ለማስታዋስ የአድዋ ሰዎች  “ዓኾ ዓኾኋይ ሆይ ሆያዬ ንጎናይ በርሆ” በማለት ደመራውን በመዞር በያመቱ  እስካሁን ያስታውሱታል። ይህም  ማለት፥ “ የቀረው በመላ ኢትዮጵያ ያለው ህዝባችሁ ገናናውን የፖርትጋልን መንግስት ተቀብሎ  እየተገዛ ነው። እናንተ ብቻ ናችሁ ከኢትዮጵያ ህዝብ ተቆርጣችሁ የቀራችሁ” እያሉ ይዘልፏቸው ስለነበረ፥  “እኛ ኢትዮጵያውያን የተቆረጣችሁ እየተባልን በገዛ አገራችን ስንሰደብ ብንኖርም፥ ዛሬ በዚህ ችቦ የነጻነት ብርሃን በራለን” እንደ ማለት ነው “ንጎናይ ማለት “ቆራጣ ማለት ነው” ሲሉ ሰምቻለሁ። የትግርኛውን ቋንቋ ስለማላውቀው አነጋገሩ ሊበላሽብኝ ይችል ይሆናል። መንፈሱ ግን እንደገለጽኩት ነው።

በዚህ ሁሉ መከራ ለአገራቸውና ላንድነታቸው ጸንተው የቆሙ የትግራይ ሰዎች በአማረኛ አሽከት፤ በትግርኛ ጾጎት የምትባለውን የመጣበቅ ባሕርይ ያላትን ሐርግ  ደመራው በሚከበርበት እለት በራሳቸው ላይ ያስራሉ። ሐረጓን ያንድነታቸውና የጽኑ መተማመናቸው ምልክት አርገው ተጠቅመውባትል። በአሽክቷ የተጠቀሙበትን ምሥጢር መስከረም ፲፮ በያመቱ “ ጽንዒ”  እያሉ ያስታውሱታል” እያሉ ሊቃውንት አበው ሲናገሩ ሰምቻለሁ።  በዚያ አካባቢ ተወልዳችሁ ያደጋችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ! ውሸት ነው ወይስ እውነት? ለቋንቋው አቀራረብ  ይቅርታ እየጠየቁ የማቃናቱን ኃላፊነት ባካባቢው ለተወለዳችሁ ለትግራይ  ልጆች ወገኖቼ እተወዋለሁ።

የቤተ ክርስቲያንን አበው ሊቃውንት ፖርቹጋሎች በኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈጽሙት ንቀትና እየከፋፈሉ እርስ በርሱ  በማጣላትና በማገዳደል የሚፍጽሙት ደባ  እጅግ እያሳሰባቸውና እያስጨነቃቸው መጣ።  ይህን ነገር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እነዚህን ትኋኖች እንዴት እንደሚገላገሏቸው አጠኑ። የመስቀሉን በዓል እንዴት እንደሚጠቀሙበት ዘዴ አመነጩ።

## የተጠቀሙበት ዘዴ

ምሥጢር ማደላደል በሚባለው ጉባዔ ላይ በየኔታ ፍስሐ መሪነት፥ ነፍሶቻቸውን ይማርና የኔታ አንዳርጌና የኔታ አምዴ የቅኔ መምሕራን ሲነጋገሩ እንደሰማሁት፥ በዚያ ዘመን የነበሩ ሊቃውንት እንዴትና

በምን መንገድ ፖርቹጋሎችን ላንድ ጊዜና ለመጨረሻ ጠራርገው ለማጥፋት ሲያስቡ፤ በመጽሐፈ መሳፍንት ምዕ ፱ ከቁጥር ፳ ላይ ያለው "ለትጻዕ እሳት እምቤተ አቤሜሌክ፥ ከመ ትብላእ አብያተ ሴኬም፥ ወትሜሎም። ወለእመ አኮ እሳት ትጻእ እምቤተ ሴኬም ወትሜሎም ከመ ትብላዕ ቤተ አቤሜሌክ" የሚለው ንባብ ትዝ አላቸው።

ይህም ማለት "በገዛ አገራችን ከውጭ እየተጎተቱ የመጡብን ፖርቱጋሎች አሁን የሚያሳዩን ንቀት ከቀጠለ ወደ ልጆቻችን የሚተላለፍ ዘላለማዊ ውርደት ነው። ልጆቻችን ተገቢ የሆነ ውርስ መስሏቸው ይቀበሉታል። ስለዚህ ሰላም ሳይኖረን ክብር ሳይኖረን ነጻነት ሳይኖረን የዘንድሮውን የመስቀል በዓል "እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሰን፤ አደረሳችሁ በመባባል እራሳችን አናታል። ይልቁንስ "የነጻነት ብርሃን ለማየት እንጠቀምበት" ብለው የተደበቀውን መስቀሉን ለማግኘት ቆርጣ እንደተነሳችው እንደ እሌኒ ወሰኑ "ከያንዳንዳችን ቤት እየተጫረች የምትወጣ የዘንድሮው የመስቀል በዓል እሳት፥ በሸርና በሸፍጥ በእርዳታ ስም መጥተው የወረሩንን ፖርቹጋሎችን ትብላ! ለአገራችን ለነጻነታችን መታገላችን በአምላክ ዘንድ ተቀባይነት አጥቶ ረድኤቱን ከነፈገንም ለዘላለም በፖርቹጋሎች ሥር ተጠቅተን ከመኖርና ለልጆቻችንም የተገዥነትን ውርስ ከማውረስ እኛኑ ትብላን" ብለው በፖርቱጋሎች የተቀበረውን አንድነታቸውን ክብራቸውንና ቦታቸውን መልሰው ለማግኘት ቆርጠው ተነሱ።

"የመስቀል በዓል ፖርቹጋሎችን የማይደምር የኛ የኢትዮጵያን የግላችን ነው። የምናከብረው ሌሊት ነው። በበዓላችን የማይደመሩት ፖርቹጋሎች እንቅልፍ ላይ ይሆናሉ። እናንተ ቱኋኖች ከአገራችን ውጡ፥ እያልን በምናበራው ችቦ ቤታቸውን እያቃጠልን በኛ ላይ የሚያደርጉትን ግፍና፥ በቅኝ ግዛት ለመቀጠል ያላቸውን ረዥም እቅድ ይህችን የመስቀል በዓል በመጠቀም ላንድና ለመጨረሻ ጊዜ መግታት አለብን" ብለው ያቀዱትን በየደብሩ ለሚኖረው አካለ መጠን ለደረሰ ወንድ ልጅ ሁሉ ትድረስ ብለው ካህናቱ ህዝበ ክርስቲያኑን በቆራጥ መንፈስ ቀሰቀሱት። መልእክቱ የደረሳቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ በመተባበርም ተግባራዊ አድርገውት አደሩ። ካህናቱ ለወገን መጎሳቆል ተቆርቁረው ወስነው ባንድ ልብ እንሙት ብለው መነሳታቸው ያስደነቀው አንድ ሰው፡-

"ካህን ሞተ ተብሎ አይነግሩም አዋጂ

እንዲህ በየደብሩ መላክ ነበር እንጂ" ብሎ እንደገጠመ ይነገራል። በነገራችን ላይ የኔታ አንዳርጌ ከላይ የጠቀስኩትን ታሪክ መሠረት በማድረግ በደመራ ሌሊት መወድስ ዘርፈውበት፥ እኛ ተማሪዎችም የሳቸውን ቅኔ እንደ ምሳሌ (ሞዴል) በመጠቀም የሳምንቱ የቅኔ መቁጠሪያችን ሆኖ መሰንበቱን አስታውሳለሁ።

ከዚህ በታች ያለው ክፍል በካህናት በያመቱ በደመራው ላይ የሚደርስ ስርአተ ጸሎት ነው። በግእዝ በመሸፈኑ ምእመናኑ ይቅሩና እኛ ካህናቱም እረስተነዋል። ለመረዳት ለመገንዘብ ከመጣር ይልቅ ባልተረዱና ባልገባቸው ነገር ለስድብና ስም ለማጥፋት የፈጠኑ ወጣቶች፤ የሚሰጡንን ስም የሚሰነዝሩብንን ስድብ ሸሽተን "በምናውቀው አናፍርም፤ በማናውቀው አንደፍርም" የሚለውን ያባቶቻችንን ሥነ ልቡና መዘንጋቱ የበለጠ ይከብደኛል።

በዚህ ዘመን ያላችሁ ማገናዘብ የምትችሉ ኢትዮጵያ ወገኖቼ ሆይ! በደመራው እለት የሚባለውን ባጭሩ ከዚህ በታች ተርጉሜ ለማቅረብ ሞክሬያለሁና በትእግስት ተመልከቱት።

የደመራውን ስርአት የጀመሩት ሊቃውንት ይህን ቆራጥ ውሳኔ ከመፈጸማቸው በፊት በነግህና በመንፈቀ ሌሊት በዚህ ጸሎት እራሳቸውን አዘጋጁ። “ስማዕ እግዚኦ እለ ኪያከ ይስእሉ:: እግዚኦ እለ ዘንስእለከ ኢንሰተት አላ በስክየት ዲበ ጸላኢነ ነሀሉ:: ሀበነ ዘወትር ጸሎተነ እምኒጠተ ጸላኢ ንትአቀብ:: . . . . ተወከፍ ሲሩያነ በምሕረትከ አንጽሕ አብዳነ አጥብብ ወጎጉላነ”(ዘነግሕ):: በማለት ጸለዩ:: ማለትም፥ “አቤቱ በቅን ሕሊና የምንለምንህን ስማ፥ የምንለምንህ እኛም ተሸንፈን እንዳንወድቅ እርዳን።በወቀሳም በከሰሳም የምንከሰስበት እንዳይኖር ብንከሰስም እንድንረታ እርዳን። ከጠላት ሽፍጥና ማታለል ነቅተን እንድንጸልይ እርዳን። በስሕተታቸው ተጸጽተው የተመለሱትን ወገኖች ተቀበላቸው። አርቆ የማሰብ ችሎታ ያጠራቸውንም ወገኖች ሕሊናቸውን ብሩህ አርግላቸው። ወደ ጠላት ጎራ በመግባት ከመካከላችን የጠፉትንም ወገኖች ንቃቱንና ማስተዋሉን ስጣቸው” ማለት ነው።

በመንፈቀ ሌሊትም “መዝገበ ጽልመት እንተ ብነ በሥምረተ አቡከ አብራህከ ለነ ዘአውጻእከነ እማዕምቅ ውስተ ብርሃን። ወወሀብከነ ሕይወተ እሞት።ወጸጎከነ እምግብርናት ግዕዛነ:: ዘበመስቀልከ አቅረብከነ አምላክ። አላ ብርሃነ ሀበነ”(መንፈቀ ሌሊት)። እያሉ ጸለዩ። ማለትም፥ “በጨለማ ውስጥ ለነበርን ለኛ ባባትህ በጎ ፈቃድ የደኅንነት ብርሃን አበራሕልን። ከጨለማ አዘቅት አውጥተህ ወደ ብርሃን አፋፍ አወጣህን። ከሞት አድነህ ሕይወትን ሰጠኸን። ከመገዛትም ነጻ አወጠሀን። በመሰቀልህ ያቀረብከን አምላክ ሆይ ብርሃንህን ስጠን”።

በግራኝ መሐመድ የተጎዳውና የተጎሳቆለው ወገን፥ በመቋቋም ላይ ሳለ እንደገና ከፖርቹጋሎች ጋራ ፊት ለፊት በመጋፈጥ የሚደርስበትን መከራ እንዳያከብድበት “ዕቀብ ኩልነ ዘእንበለ ጻሕብ ወዘእንበለ ተመውዖ ወዘእንበለ ማዕቀፍ:: አድኅነ አእጋሪነ እምዳህጽ ወአዕይንቲነ እምአንብእ ወነፍስተነ እሞተ ኃጢአት ወደምረነ ምስለ እለ ድኅኑ ብከ በጸሎተ ኩሎሙ እለ እምዓለም አሥመሩከ” የሚለውን ንባብ ያቀፈውን ሊጦን ጸለዩ። (ሊጦን ዘሠርክ) ይህም ማለት፥ “አምላካችን ሆይ! በፍልሚያ ውስጥ ገብተን ስንዋጋ ተደናቅፈን ከመሸነፍ ጠብቀን። ጠላቶቻችንን ስናሳድድ አንዳልጦን ከመውደቅ ደግፈን። በውርደትና በንቀት በሚያደርሱብንም መካራ አንገታችንን ደፍተን ከማዘን ከመተከዝና እንባ ከማፍሰስ፤ ተዋርደን ከመሞትም አድነን። ባንተ ታምነው ባንተ መከላከል ከሚድኑት ጋራ ደምረን”

ከዚያም በማስከተል ከነቢዩ ዳውት ድርሰት (መዝ ፶፱፡፩-፫) ላይ ከዚህ በታች የሰፈረውን

| ግእዝ | አማረኛ |
|---|---|
| “እግዚኦ ገደፍከነ ወነሠትከነ፥ | አቤቱ ረሳህን? አፈረስከን |
| ቀሠፍከነሂ ወተሣህልከነ | ቀጣኸን ይቅርም አልከን |
| አድለቅለቃ ለምድር ወሆካ | ምድርን አናወጥካት ቀጣሀትም |
| ወፈወስካ ቁስላ እስመ አንቀልቀለት | ተናውጣለችና ቁስሏን ፈወስክ |
| አርአይኮሙ ዕጹባተ ለሕዝብከ | ለህዝብህም ጭንቅን አሳየሀቸው |
| ወአስተይከነ ወይነ መደንግጸ” | አስደንጋጭ ወይንን አጠጣሀን |

የሚለውን በክስተት መልክ ከተቀባበሉ በኋላ፤ ከዚያ ቀጥሎ ያለው ንባብ “ወወሐብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ ከመ ያምሥጡ እምገጸ ቅስት ወይድኅኑ ፍቁራኒከ” የሚለውን ዲያቆኑ መስቀሉን ይዞ ከፍ ባለ ድምጽ አሰምቶ እንዲያዜም አደረጉ።

ይህም የሚገልጸው ለደመራ በዓል የችቦውን እሳት ከፖርቱጋሎች ጦርነትና ጥቃት ወዳጆችህ እናመልጥ ዘንድ የመገላገያ ምልክት (ዘዴ) አድርገን እንድንጠቀምበት፤ ለምንፈራህ ጥበቡን ገለጽክልን" የሚል መንፈስ የያዘ ነው::

ደመራውም ሆነ ችቦው ህዝባዊ ምልክትነትና ውክልና አላቸው። ችቦው ከተበታተኑ ጭራሮዎች የሚሰራ ነው። ኢትዮጵያዊነት፤ የሚደመረውም እንጨት በቤት ወከፍ ከየቤቱ የተሰበሰበ ነው። ይህ የደመራው በዓል በሰረዝነት ባህርይ የተሸከመውን በታሪክ ቅኔ የበለጸጉ አባቶች አንድ ላይ ተሰብስበው ቅኔውን ሲያመሰጥሩ ይናገሩታል እንጅ ለሕዝብ አልተነገረም። የደመራውን በዓል ሙሉ ታሪክ የመግለጽ እዳና ግዴታ ያለባቸው በጉባዔ የዋሉ ናቸው ያልኩት በዚህ ምክንያት ነው። ለህዝብ የሚነገረው የታሪኩ መሰረት የሆነው እሌኒ እንዴት፤ መቼና ለምን እንደ ጀመረችው ብቻ ነው።

አምና ለዘመነ ሉቃስ <u>"የተወደደችውን የጌታን ዓመት እንስበክ"</u> በሚል ርዕስ ባቀረብኳት ጦማር ላይ ስለ መንፈሳዊ አባት ስገልጽ tp://www.medhanialemeotcks.org/pdf/ " ይመልከቱ። አምላኩን ወዶ ለማስወደድ፥ ሃይማኖቱን አክብሮ ለማስከበር፡ በህዝባዊ ፍቅር ልቡ የነደደ፥ ቅዱስ ተብሎ የተሰየመ አባት፡ የምሕረት ምንጭ በሆነው አምላክ ስም፡ በሚያቀርበው የምሥራች ቃል ዘመኑን ባርኮ ለሥጋውያን መሪዎች አውደ ምህረቱ ይለቅ ነበር" እንዳልኩት፥ በደመራው በዓልም፥ ካህኑ ችቦ በእጁ ጨብጦ"ደምረነ ምስለ እለ ይድኅኑ" ብሎ ጸሎቱን አድርሶ የመጀመሪያዋን እሳት ይጭራታል። ካህኑ ካቃጣላት ችቦ ላይ የአገሪቱ ሥጋዊ መሪ በራሱ ችቦ እሳቱን እንዲለኩስ ፈቅድለታል። የአገሪቱ መሪም በችቦው ለኩሶ በደመራው ላይ መለኮሱን ይመራል። በተዋረድ የተከበሩ የአገር ሽማግሌዎች ይቀጥላሉ። ከዚያ ጎረምሳው፥ ኮበሌው ወጣቱ እሳቱን በችቦው እየተቀባበለ ወደ ደመራው እየወረወረ የጀግንነት ምልክቱን ብትር ከፍ አድርጎ ይዞ ሆ! እያሆ አሆሆ እምቢ በል ! ያለ ደመራውን ይዞራል። ለውርደት ለመገዛት እምቢተኝነትና ያሳያል። ቁርጥ የሚባል ስም ተሰጥቶት ጥሬ ሥጋ መብላት የተጀመረውም በዚሁ ዘመን ነው።

በሌሎች ክፍላተ ሐገሮች የሚደረገው ተመሳሳይ መሆኑንና አለመሆኑን ባላውቅም፥ ባደኩበት አካባቢ ቁርጥ ሥጋ ወንዶች ብቻ ሲበሉ እንዳየሁ ሁሉ፥ በደመራው በዓልም ዳቦት(ችቦ) አብርተው ከቤት የሚወጡት ወንዶች ብቻ ናቸው። ወንዶች ብቻ የሆኑበትን አባቶች ሲናገሩ እንደሰማሁት፥ "ብርሃን ዘበ አማን ዘያበርህ ለኩሉ ሰብዕ" የተባለው በጨለማ ለነበረው ዓለም ያበራው፥ ያለ ወንድ ዘር ወንድ ሆኖ የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለማሳየት ሲሆን፤ ወደ ባህላችን ስንመነዝረው የነጻነት ብርሃን ለማሳየት የመዘጋጀት ኅላፊነት ያለባቸው ወንዶች እንደሆኑ ለማሳየት ነው።

እመቤታችን <u>"እመ ብርሃን (የብርሃን እናት) ምሥራቅ (መውጫ)"</u> በመሆን በማሕጸኗ አድሮ ወልዳው ታቅፋ በሲና በርሀ ያቋረጠችውን የመከራ ዘመን፤ ኢትዮጵያውያን በደመራው በዓል እስካቆሙት ድረስ በፖርቱጋሎች የደረሰባቸውን መከራ ያስታውሱታል። <u>ከፖርቹጋሎች ጋራ በተፈጠረው ታሪካዊ ክስተት ላይ፥ በዚያች ሌሊት ችቦ እያበራ ወጥቶ ፖርቱጋሎችን የደመሰሱት ወንዶች ብቻ ስለሆኑ፥ የመታሰቢያነቱ ገጽታ ተለጥጦ መልኩን እንዳይለውጥ ሴቶች ችቦ አብርተው ከመውጣት ተቆጥበዋል።</u> በፖርቱጋሎችና በነሱ መካከል የነበረውን መሰዳደብ ለማስታወስ በተቀጣጠለው ችቦ ከምድጃ፤ ከጓዳ፤ ከጋጥ ከበረት ጀምረው በየስርቻው እየገቡ <u>"ትኋን ውጪ ቁንጫ ግቢ"</u> ይላሉ። እስከዚህ የገለጽኩት ለህዝብ ተብራርቶ ባይቀርብም ከላይ እንዳልኩት በያመቱ በየደመራው በዓል ላይ አመታዊ ሥርዓት ሆኖ ይካሄዳል። ይህም ጤፍን፤ እንጀራንና ቁርጥ ሥጋ እንዴት፤ መቼና እንዴት እንደተጀመረ ሳናውቀው እንደምንበላው ማለት

ነው። ይህ በእሌኒ የተጀመረ በዓል፥ በኢትዮጵያውያን ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደሐረግ እየዘመተ በቅኝ ገዥዎች ሳይቆራረጥ በደማችን በምግባችን በስሜታችን ሳይቀር ተቀርጾ ለረዥም ዘመን በመቀጠሉ፥ የታሪክና የባሕላችንን ምዕራፍ እያሰፋ እስከኛ ዘመን ደርሷል። ትውልድ በውጭም ሆነ ባገር በቀል ወራሪዎች ተወሮ፥ ተበታትኖና ቋንቋውን ታሪኩንና ባሕሉን እንዲረሳው ካልተደረገ፥ ታሪኩ በግልጽ እየተነገረው በያመቱ ከቀጠለ፥ እየተፈራረቀ የሚገጥመውን ሁሉ እያባዛና እየደመረ የነበረውን ባህሉንና ታሪኩ እያሰፋ፤ ክብሩንና አንድነቱን በመጠበቅ ይቀጥላል::

የጥንት ኢትዮጵያውያን ከወገኖቻቸው አንድ ሰው ሳይጎዳ በመስቀሉ የችቦ እሳት አገራቸውንና ነጻነታቸውን ከፖርቱጋሎች ነጥቀው መለሱ። የፖርቹጋሉን መሪና የሮማውን ፓፓ ሸፍጥ አከርካሪውን የሰበሩበት ጥበብና ጀግንነት፤ ፖርቹጋሎችንና ሮማውያን አሳፍሮና አውርዶ ቢያባርርም፥ በየዘመኑ የሚያመረቅዝ ቂም አትርፏል።

<u>ከታሪካችን ጋራ ያለው ጥምረት ለትውልዱ በግልጽ እየተነገረ እንዲቀጥል፥ ጠንካራ መመሪያ የመስጠቱ ኃላፊነት የመንፈሳዊና የፖለቲካ መሪዎች ቢሆንም፥ ከመንግሥት ይልቅ በላቀ ሁኔታ ኃላፊነቱ የሚመለከታቸው ወላጆችን ነው።</u> የዘንድሮው ደመራስ ምን ዝክረ ነገር (<u>Social Memory</u>) አትርፎልን አለፈ?

# <u>የዘንድሮው አጋጣሚ</u>

ባንድ ወቅት የተዘጋጁ መጻሕፍት በውስጣቸው የያዙትን ምዕራፍ በሚገጥሟቸው ተመሳሳይ አዳዲስ ክስተቶች እየሰፉ በመደጋገም እንደሚታተሙ፥ በየአመቱ በመመላለስ የሚታወሱ ሁሉ በዓላት፥ በየደረሱበት የዘመን ርከን፤ የሚገጥሟቸውን በመደመር ይዘታቸው እየሰፋ የሕብረተ ሰቡን ትዝታ፤ ድካምና ብርታት ያለፈበትን ሁሉ ውጣ ውረድ ዝክረ ነገር (Social Memory) የተሸከሙ ናቸው።

<u>እሌኒ</u> እሳቱን ያነደደችው የተቀበረውን መስቀል ከተቀበረበት ፈንቅላ እንዳወጣቸው፤ የእኛ አባቶችም ፖርቱጋሎች የጫኑባቸውን ውርደትና መከራ ፈንቅለው ለመውጣት "ለትጻዕ እሳት እምቤተ አቤሜሌክ፥ ከመ ትብላእ አብያተ ሴኬም፡ ወትሜሎም:: ወለእመ አኮ እሳት ትጻእ እምቤተ ሴኬም ወትሜሎም ከመ ትብላዕ ቤተ አቤሜሌክ" ብለው እንደተነሱ ዝክረ ነገራችን ያስገነዝበናል። ይህም ማለት <u>ከያንዳንዳችን ቤት እየተጫረች የምትወጣ የዘንድሮው የመስቀል በዓል እሳት፥ በሽርና በሸፍጥ በእርዳታ ስም መጥተው የወረሩንን ፖርቹጋሎችን ትብላ! ለአገራችን ለነጻነታችን መታገላችን በአምላክ ዘንድ ተቀባይነት አጥቶ ረድኤቱን ከነፈገንም ለዘላለም በፖርቹጋሎች ሥር ተጠቅተን ከመኖርና ለልጆቻችንም የተገዥነትን ውርስ ከማውረስ እኛኑ ትብላን" ብለው ቆርጠው ተነሱ።</u>

<u>እኛም በዘመናችን</u> ዛሬ፡-

"የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርሀ ግብር ለሚመለምላቸው ቀሳውስት ዘረጋ። የማሰልጠኑ ዓላማ ቤተ ክርስቲያናን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው።" የሚል ፖርቱጋሎቹ ያቃዱትን የሚመስል አገራችንና ቤተ ክርስቲያናችን ተብትቦ የያዘ መርሆ እንደዘረጉብን እነ

ዶ ክተር አረጋዊ በርሄ ወያኔዎች እርስ በርሳችን እንድንጠፋፋ መረብ ማፍረሻ፤ ለተበተቡብን ችግር መፍቻ አርገን ልንጠቀምበት ይህ ዘመን ይጠይቀናል። ሰላማችን በደፈረሰበት በዚህ ዘመን "እንኳን ለብርሀነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን" ማለት ራስን ማታለል ነው።

ዛሬ ልብሱን ቆቡን መስቀሉን በእጃችን ጨብጠን በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የተሰገሰግን አስመሳይ ሰባኪ(ቂ)ዎች ህዝብ የሚቃጠልበትን እሳት እየለኮስን ህዝብን ለማቃጠል ለተሰለፉ ሰዎች በማቀበል ላይ ነን። ከሁሉም የሚያሳዝነው የደመራው ችቦ መብራት የመታሰቢያነቱ ገጽታ ተለጥጦ መልኩን እንዳይለውጥ ሴቶች ችቦውን አብርተው ከመውጣት ተቆጥበው ችቦውን የሚያበሩት ወንዶች ብቻ ነበሩ። ዛሬ የነገር የአድማና የጥላቻ ችቦ በየአውደ ምህረቱ የሚያቀጣጥሉ ሴቶች ያውም ልጃገረዶች ሆኑ። በባህላችን ሴት ልጅ በማታውቀው ነገር ያውም በአውደ ምህረት ላይ ይህን የመሰለ መረን የለቀቀ ጠባይ ማሳየት ቀርቶ፤ እንደ ልጃገረድ ዓይን አፋር ነው እየተባለ ትህትና እጅግ የሚታይበት የወንድ ባህርይ መግለጫዎች ነበሩ።

ዛሬ እልልታውን ጭብጨባውን እያቀለጡ፤ ከበሮውን (መምታት አይባልም) እየደለቁ የእውነት ማፈኛ አርገው በዓውደ ምህረት ላይ ተሰለፉ ። ይህን ስል በአሜሪካ ዙሪያ ያየኋቸውን ለመግለጽ እንጅ፤ በንጹህ መንፈስ፤ በመንፈሳዊ ቅናት፤ በትህትና ከልባችሁ በማገልገል ያላችሁ አይመለከታችሁምና የምናገረው ሊሰማችሁ አይገባም። ያም ሆነ ይህ፤ ይህ በዘመናች የተከሰተው ጉድ፤ ያለንበት ዘመን በጣም ከፉ! እጅግ በጣማ ከፉ! መሆኑን ከምንረዳባቸው ምልክቶች አንዱ ነው።

አባቶቻችን በተቀጣጠለው ችቦ ከምድጃ፤ ከጓዳ፤ ከጋጥ ከበረት ጀምረው በየስርቻው እየገቡ "ትኋን ውጪ " እያሉ ፖርቱጋሎችን ጥርግርግ አድርገው እንዳስወጡ፤ በየ ቤተ ክርስቲያኑ በየመንደሩ በየቤቱ መስለው ገብተው በህዝቡ ላይ እሳት በማንደድ ላይ ያሉትን በመተባበር ከመካከላችን ለማስወጣት የምንፈተንበት ጊዜ ነው።

በእውነት ላይ በቆሙት ወገኖች ላይ የሚነደው እሳት እኔን አይመለከተኝም ብሎ ቆሞ የሚመለከት ካለ፤ በኃጥአን የሚነደው እሳት የሚለቀን አይደለም። የሚካሂድ ጥፋት እንዳለ እያወቀን፤ አጥፊውን ከመገሰጽ ይልቅ ልማዱ አይታጎል እንጅ እኔ ምንቸገረኝ በማለት፤ የደመራው ዝክረ ነገር በሚመራን መንገድ የደመራውን በዓል የማናከበር ከሆን፤ ቅዱስ ያዕቆ ብ እንዳለው፤ በፊቱ ላይ ያለውን ጉድፍ ለማስወገድ የማይጠቀምበትን መስተዋት በፊቱ እንደሚዘረጋ ሞኝ መሆናችን ነው።

የደመራውን በዓል ዝክረ ነገር እንዳይረሳ በሰላም ጊዜ በማክበር ማስተዋሱ ማልካም ነው። ይሁን እንጅ፤ በያመቱ የደመራውን በዓል ስናከብር እንዳባቶቻችን ከችግር ለመውጣት የማንጠቀምበት ከሆነ ምን ይጠቅማል? በሰላም ጊዜ መሳሪያ የሚታጠቅ ሰው ስለታጠቀ ብቻ ሊተኩሰው አይደለም። ወቅቱ ሲያስገድድ የታጣቂው መንፈስ ይቀየራል። የመሳሪያውንም አያያዝና አቅጣጫውን ይቀይራል። የነበልባሉን ፍላጻ መመታት በሚገባው አካል ላይ ያነጣጥራል። የደመራው ዝክረ ነገር የሚነግረን ይህንን ነው።

ከሚድኑት ጋር አንድ አድርገን "ደምረነ ምስለ እለ ይድኅኑ" እያሉ በእምነት በሥነ ልቡና በህብረት እየታገሉ ቤተ ክርስቲያናችንን ያስረከቡን ያባቶቻችን አምላክ ረድኤቱን አይንፈገን! ይህ ዘመን አልፎ "እንኳን በሰላምና በጤና አደረሰን" ለመባባል ያብቃን።